በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ፅ/ቤት ቤት የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች
የ2018ዓ.ም የአንደኛ መንፈቅ አመት የአካባቢ ሳይንስ ሞዴል ፈተና ።

የጥያቄ ብዛት፡ 40
የተፈቀደ ሰዓት፡ 1 ሰዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የአካባቢ ሳይንስ ፈተና ነው።

በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል ፤ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ መስጫ ደተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ የሰጣል ።በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል ።መልስ የሚሰጠው ለብቻ በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤ በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደምብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደምብ በማጥፋት መፅዳት አለበት።

መልስ የሚሰጠው በመልስ መስጫው ላይ ብቻ ነው ፤ ለምሳሌ መልሳችሁ ለ ከሆነ ከታች በሚታየው መልክ ማጥቆር አለባችሁ ።

ሀ ለ ሐ
መ ○ ● ○ ○

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1ሰዓት ነው።ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመፃፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራትማቆም አለብን ።ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቁ አለብን ።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም ፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል ።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባጨውን መረጃዎች በሙሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ።

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !

LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ፡ ከተራ ቁጥር 1-40 የሚገኙትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል በይበልጥ ተስማሚ የሆነውን መልስ በመምረጥ በመልስ መስጫው ወረወት ላይ አጥቁሩ።

1. የኢትዮጵያ አንፃራዊ መገኛ ከኬንያ አንፃር በየትኛው አቅጣጫ ትገኛለች ?

ሀ. በስተደቡብ　　　　ለ. በስተ ሰሜን

ሐ. በስተ ምስራቅ　　　　መ. በስተ ምዕራብ

2. ከሚከተሉት ውስጥ የኢትዮጵያ አጎራባች ሃገር የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ጅቡቲ　　　　ለ. ግብፅ

ሐ. ናይጄሪያ　　　　መ. ኮንጎ

3. የጥያ ትክል ድንጋይ ፍፁማዊ መገኛ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. $14^0$ 7’ 47’’ ሰሜን ኬክሮስ እና $38^0$ 43’ 60’’ ምስራቅ ኬንትሮስ

ለ. $9^0$ 48’ 58’’ ሰሜን ኬክሮስ እና $38^0$ 36’ 35’’ ምስራቅ ኬንትሮስ

ሐ. $8^0$ 25’ 58’’ ሰሜን ኬክሮስ እና $38^0$ 36’ 35’’ ምስራቅ ኬንትሮስ

መ. $8^0$ 25’ 58’’ ሰሜን ኬንትሮስ እና $38^0$ 36’ 35’’ ምስራቅ ኬክሮስ

4. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ንድፍ ካርታን ለማዘጋጀት የማያስችለው መመሪያ የቱ ነው ?

ሀ. የቦታዎችን መነሻ ማስቀመጥ

ለ. የቦታውን ንድፍ ካርታ በሃሳብ ማስቀመጥ

ሐ. የሚሳለውን ካርታ ድንበር አለመወሰን

መ. በተዘጋጀው ካርታ ላይ ወሳኝ መረጃዎችን መፃፍ

5. ከሚከተሉት ውስጥ የካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ጎግል ኧርዝ　　　　ለ. ጎግል ካርታ

ሐ. የቦታ እና አቅጣጫ ማሳያ　　　　መ. ቴሌግራም

6. ምግብ በጊዜያዊነት የሚከማችበት እና ምግብ የሚፈጭበት የስር ዓተ ልመት አካል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ጨጓራ　　　　ለ. ጉሮሮ　　　　ሐ. አፍ　　　　መ. ሬብ

LIVEWORKSHEETS

7. ከሚከተሉት ውስጥ ቁስ አካል ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ብረት　　ለ. ድንጋይ　　ሐ. ጉልበት　　መ. ውሃ

8. ሁለትና ከሁለት በላይ ከሆኑ ንጥረ ነገሮች በኬሚካዊ መስተጋብር የሚፈጠር ልዩ ቁስ ምን ይባላል ?

ሀ. ድብልቅ　　ለ. ንጥረ ነገር

ሐ. አቶም　　መ. ውህድ

9. ከሚከተሉት ውስጥ የጨው ምሳሌ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ውሃ　　ለ. ሶዲየም ክሎራይድ

ሐ. ናይትሪክ አሲድ　　መ. ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ

10. ከሚከተሉት ውስጥ የጉልበት ምንጭ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ፀሃይ　　ለ. ውሃ　　ሐ. ንፋስ　　መ. ሁሉም

11. የይዘት ዓለማቀፋዊ አሐድ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ሜትር　　ለ. ካሬ ሜትር

ሐ. ኪሎግራም　　መ. ኪዩቢክ ሜትር

12. ከሚከተሉት ውስጥ ድምጽ በአነስተኛ ፍጥነት ማስተላለፍ የሚችለው የትኛው ነው ?

ሀ. አየር　　ለ. ውሃ　　ሐ. ብረት　　መ. ወና

13. የአየር ንብረት ይዘት ውስጥ የሚመደበው የትኛው ነው ?

ሀ. ከፍታ　　ለ. ደመና　　ሐ. ሙቀት　　መ. ኬክሮስ

14. በጣም ሞቃታማ እና ደረቃማ የሆነ የአየር ንብረት ክልል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ደጋማ　　ለ. በረሃማ　　ሐ. ውርጫማ　　መ. ቆላማ

15. በአንድ ቦታ የፀሃይ ጨረር በቀጥታ የሚያርፍ ከሆነ ጨረሩ የሚያርፍበት ቦታ ምን ይሆናል ?

ሀ. መጠኑ ከፍተኛ ይሆናል　　ለ. መጠኑ አነስተኛ ይሆናል

ሐ. መጠኑ በጣም ከፍተኛ ይሆናል　　መ. መጠኑ ይሰፋል

LIVEWORKSHEETS

16. ትላልቅ ቅንጣጢቶችን በውስጡ የያዘ የአፈር አይነት ........... ይባላል ።

ሀ. ሸክላ አፈር ለ. አሸዋማ አፈር

ሐ. ለም አፈር መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

17. ከሚከተሉት ውስጥ ተመራማሪዎች ስለተለያዩ በሽታዎች መከሰት ትንበያ ለመስጠት ያሚያስችል የካርታ መተግበሪያና መፈለጊያ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ጎግል ኸርዝ ለ. ጂፒኤስ

ሐ. ንድፍ ካርታ መ. ጎግል ካርታ

18. የምስራቅ አፍሪካን አንፃራዊ መገኛን ለመግለጽ የሚያገለግለው የቱ ነው ?

ሀ. ውሃማ አካላት ለ. ታዋቂ ቦታዎች

ሐ. ኬክሮስ መ. አጎራባች ሀገራት

19. የአርክቲክ ክበብ የሚገነው በስንት ዲግሪ ላይ እና በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

ሀ. $23^{1/2}$ ሰሜን ለ. $23^{1/2}$ ደቡብ

ሐ. $66^{1/2}$ ደቡብ መ. $66^{1/2}$ ሰሜን

20. ከሚከተሉት ውስት የምስራቅ አፍሪካ ሀገር የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ሊቢያ ለ. ማሊ ሐ. አልጄሪያ መ. ዩጋንዳ

21. ፈሳሽ ከሆነ ፕላዝማ እና ከደም ህዋሶች የተሰራ አካላችን የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ልብ ለ. ደም ሐ. ሳንባ መ. ኩላሊት

22. ከሚከተሉት ውስጥ በትክክል የተዛመደው የደም ህዋስ የቱ ነው ?

ሀ. ቀይ የደም ህዋስ ........... ኦክስጅን መሸከም

ለ. ነጭ የደም ህዋስ ........... ኦክስጅን መሸከም

ሐ. ፕሌትሌቶች ..................... በሽታ መከላከል

መ. ቀይ የደም ህዋሶች ........... በሽታ መከላከል

LIVEWORKSHEETS

23. በኦክስጅን የበለፀገ ደምን በኣኦርታ ውስጥ ወደ ተለየዩ የሰውነት ክፍሎች የሚረጨው የልብ ክፍል የቱ ነው ?

ሀ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ለ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

ሐ. ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

መ. ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

24. ከሚከተሉት ውስጥ የልብ ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ደም መርጨት

ለ. ኦክስጂን ለህዋሳት ማድረስ

ሐ. የተቃጠለ አየር ከሰውነት ማስወገድ

መ. ሁሉም መልስ ነው

25. ከሚከተሉት ውስጥ በወር አበባ ጊዜ ከሚከሰቱ ዋና ዋና ሂደቶች መካከል አይመደብም ።

ሀ. እንቁላል ወደ መህፀን ቦይ መግባት

ለ. እንቁላል በእንቁሊጥ ውስጥ መቆየት

ሐ. ጽንስ ባለመከናወኑ የማህፀን ግድግዳ መፈራረስ

መ. የማህፀን ግድግዳ በደም ስሮችና ሽፋን ህብረ ህዋሳት መደራጀት

26. በምጋት ጊዜ ዝቅተኛ ሆኖ በ ኢ-ምጋት ጊዜ ከፍተኛ የሚሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ

ለ. ኦክሲጅን

ሐ. ናይትሮጅን

መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

27. ስለ ልይ ዘር ድብልቅ በትክክል የሚገልፀው የቱ ነው ?

ሀ. የድብልቁ ይዘት ወጥ እና ተመሳሳይ ነው

ለ. በአይን እና አጉሊ መነፀር ምንዝሮቹን መለየት ይቻላል

ሐ. ድብልቆቹ በአብዛኛው ሙሙት ናቸው

መ. የድብልቆቹ ምንዝሮች በአይን ወይም በአጉሊ መነፀር መለየት አይቻልም።

28. የሁለት ፈሳሾች ድብልቅ ባላቸው የእፍግታ ልዩነት የምንለይበት ዘዴ ምን ይባላል?

ሀ. ንጥረት

ለ. ጥሊያ

ሐ. ቀረራ

መ. ትነት

LIVEWORKSHEETS

29. ከሚከተሉት አንዱ ታዳሽ የጉልበት ምንጭ አይደለም

ሀ. ንፋስ　　ለ. የፀሀይ ብርሃን

ሐ. ውሃ　　መ. ድንጋይ ከሰል

30. ክብደት ያላቸውን ነገሮች ለመጫን የሚጠቀመው የቀላል መኪና ዓይነት የቱ ነው ?

ሀ. ዘንባይ ወለል　　ለ. ሽብልቅ

ሐ. መፍቻ　　መ. ሽከርክሪት

31. ከሚከተሉት ውስጥ የሽብልቅ ምሳሌ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. አካፋ　　ለ. መጥረቢያ　　ሐ. ቲንሳ　　መ. ባሬላ

32. በአንድ በተወሰነ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የሚከሰት የአየር ጠባይ ድምር ውጤት ምን ይባላል?

ሀ. የአየር ግፊት　　ለ. የአየር ሁኔታ

ሐ. የአየር ንብረት　　መ. የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች

33. ከምድር ወገብ በስተሰሜን የሚገኙ የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት ዝናብ የሚያገኙት በየትኞቹ ወራት ነው ?

ሀ. ከታህሳስ እስከ ሰኔ　　ለ. ከታህሳስ እስከ የካቲት

ሐ. ከጥቅምት እስከ ሚያዝያ　　መ. ከሰኔ እስከ መስከረም

34. የአየር ንብረት በከፍተኛ ደረጃ በመቆጣጠር ተፅዕኖ የሚያሳድረው በየትኛው ላይ ነው?

ሀ. በእንስሳት　　ለ. በእፅዋት

ሐ. በአፈር አይነት　　መ. ሁሉም መልስ ነው

35. ከሚከተሉት ውስጥ ዓመታዊ የዝናብ መጠናቸው ከ250 ሚ.ሜ በታች የሆነው የአየር ንብረት ክልል የቱ ነው?

ሀ. የደጋ የአየር ንብረት ክልል　　ለ. የሐሩር ሞቃታማ የባህር ዳርቻዎች

ሐ. የበረሃ የአየር ንብረት ክልል　　መ. የሳር ምድር ሞቃታማ የአየር ንብረት ክልል

LIVEWORKSHEETS

36. ምስራቅ አፍሪካን የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት እንድትሆን ካስቻሏት ምክንያቶች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው ?

ሀ. የተለያዩ ተራራዎች ለ. የማዕድን እጥረት መኖር

ሐ. አምባ ምድሮች መ. ዝቅተኛ ስፍራዎች

37. ከሚከተሉት ውስጥ በወርቅ እና በቆርቆሮ ማዕድን አይነት የምትታወቅ ሀገር የትኛዋ ናት?

ሀ. ቡሩንዲ ለ. ኬንያ ሐ. ሶማሊያ መ. ዩጋንዳ

38. የማዕድን የማውጣት ሂደት የሚያስከትላቸው ዘርፈ ብዙ የአካባቢያዊ ጉዳት የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. የመሬት አቀማመጥን ያስተካክላል

ለ. የአየር እና ውሃ በመከል ያስከትላል

ሐ. ለአካባቢ ላሉ የዱር እንሣት ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ

መ. ለአፈር እና ውሃ ጥበቃን ያመቻል

39. ተገቢ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የቱ ነው?

ሀ. ባዮጋዝን አለመጠቀም

ለ. የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ዛፍ አለመትከል

ሐ. በቤት ውስጥ ውሃን በአግባቡ መጠቀም

መ. በወንዞች አካባቢ እፅዋትን አለመትከል

40. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ለመንከባከብ የሚያስችለው ዘዴ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ታዳሽ የሃይል ምንጮችን አለመጠቀም

ለ. የተፈጥሮ ሀብትን ያለአግባብ መጠቀም

ሐ. ሀገር በቀል እፅዋቶችን መትከል

መ. የሚታደሱ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመተካት አለመጠቀም

LIVEWORKSHEETS